የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No.37
ADDIS ABABA 11th April, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፩/፪ሺ፲፯
የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ………….
…………………................................... ገጽ ፲፰ሺ፪፻፲፬

## Content

Proclamation No.1371/2025
Environmental and Social Impact Assessment
…………………………….………… Page 18214

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፩/፪ሺ፲፯

## የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ

የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የልማት ሀሳብ ንድፈ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ሲመረጥ፣ ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በውል የታሰበውን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ፤

መንግስታዊ ሰነድ በአካባቢና ማህበረሰብ ሊያስከትለው የሚችለውን ተፅዕኖ በመለየት ገና ከመፅደቁ በፊት መገምገም፣ የመፅደቂያው ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሃዱና እንዲቀናጁ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ፤

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት ከደረሰችበት የኢኮኖሚ እድገት አኳያ የልማት እንቅስቃሴዎች በአካባቢ፣ በማህበረሰብ እና በኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ ቢቻል ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤

አሉታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖዎችን መተንበይ፤ የመፍትሔ እርምጃዎችን መውሰድና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሚነታቸውን ማዳበር፤ በሕገ መንግስት የተደነገጉትን የአካባቢ ደህንነት መብቶችንና ዓለማዎችን የመተግበርን ሂደት የሚያግዝ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO. 1371/2025

## ENVIRONNEMENTAL AND SOCIAL IMPACT ASSESSMENT PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to put in place a legal framework to predict and manage the environmental effects which a proposed development activity as a result of its design sitting, construction, operation, or an ongoing one as a result of its modification or termination, entails and thus helps to bring about intended development;

**WHEREAS,** it has become necessary to put in place a legal framework to assess the possible impacts on the environment prior to the approval of a public instrument provides an effective means of harmonizing and integrating environmental, economic, cultural and social considerations into a decision-making process in a manner that promotes sustainable development;

**WHEREAS**; it is necessary to develop a legal framework to avoid whenever possible or minimize the adverse environmental, social and economic impacts of development activities in line with the current comprehensive development stage of the country;

**WHEREAS**, the implementation of the environmental rights and objectives enshrined in the Constitution would be fostered by the prediction and management of likely adverse environmental impacts, and the maximization of their socioeconomic benefits;

የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልፅነት፣ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ፣ በአጠቃላይ እራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት ዕቅዶች አወጣጥና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሕዝቡን፣ በተለይም ደግሞ ማህበረሰቡን ለማሳተፍ የሚረዳ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፸፩/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፤ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፤ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሯዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፪/ "የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ" ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም መንግሥታዊ ሰነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው፤

፫/ "ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ" ማለት በመንግስታዊ ሰነድ ውስጥ የአካባቢና የማህበራዊ ጉዳዮች መካተታቸውን ለማረጋገጥና ከማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር ያላቸውን ትስስር ለመተንተን የሚደረግ ግምገማ ነው፤

**WHEREAS**, environmental impact assessment serves to bring about administrative transparency and accountability, as well as to involve the public and, in particular, communities in the planning of and decision taking on developments which may affect them and its environment;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby Proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Environmental and Social Impact Assessment No.1371/2025".

### 2. Definitions

Unless the context provided otherwise, in this Proclamation:

1/ "Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their qua1ity or quantity and the welfare of human or other living beings, including but not restricted to, land atmosphere, whether and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics;

2/ "Environmental and Social Impact Assessment" means the methodology of identifying and evaluating in advance any effect, be it positive or negative, which results from the implementation of a proposed project or public instrument;

3/ "Strategic Environmental and social assessment" means an evaluation that aims at integrating environmental and social consideration into public instruments and evaluate the inter-linkages with economic and social considerations;

፬/ "የአካባቢና ማህበራዊ ኦዲት" ማለት ይሁንታ የተሰጠው ፕሮጀክት በተሰጠው ፈቃድ መሠረት እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፤

፭/ "ተፅዕኖ" ማለት በአካባቢ ወይም በማህበራዊ በንዑሳን ክፍሎቹ ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በሰው ጤና ወይም ደህንነት፣ በእፅዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈር፣ በአየር፣ በውሃ፣ በአየር ንብረት፣ በተፈጥሯዊ ወይም በባህላዊ ቅርስ፣ በሌላ ቁሳዊ ቁም አካል ወይም በአጠቃላይ ሲታይ በአካበቢያዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወይም በባህላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ለውጥ ነው፤

፮/ "ማህበራዊ" ማለት የሰዎች አኗኗር እና የእርስ በእርስ ትስስር ነው፤

፯ "ማህበራዊ ተፅዕኖ" ማለት በልማት ዕቅድ ምክንያት በሰዎች አኗኗር፣ የእርስ በእርስ ትስስር ስራ፣ እንደ ግለሰብ እና የማህበረሰብ አካል የሚደራጁበት ሁኔታ ላይ የሚከሰት ተፅዕኖ ነው፤

፰/ "የፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት" ማለት እንደሁኔታው የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም የንግድ ድርጅት ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የመንግሥት ተቋም ነው፤

፱/ "ፕሮጀክት" ማለት ማንኛውም በመንግስት፣ በግል፣ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ወይም በህዝብ ሀብት ለማፍራት ወይም ለማሻሻል የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበረሰባዊ አገልግሎቶችን ለማሳደግ እና የቀጣዩን ትውልድ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተወሰነ ሀብት፣ ጊዜና ቦታ ላይ ምርትና አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚተገበር የልማት እንቅስቃሴ ነው፤

፲/ "የፕሮጀክት ባለቤት" ማለት ፕሮጀክቱ በተቋም የታቀደ ሲሆን የሚመለከተው ተቋም ወይም በግሉ ዘርፍ የታቀደ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው፤ በህዝብ ሀብት የታቀደ ሲሆን ደግሞ የተጠቀሰው ህዝብ ማለት ነው፤

፲፩/ "መንግስታዊ ሰነድ" ማለት ማንኛውም የመንግስት ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም ነው፤

4/ "Environmental and Social Audit" means a follow up and controlling action by regulatory body for ensuring implementation of an environmental and social clearance;

5/ "Impact" means any change to the environment or social to its component that may affect human health of safety, flora, fauna, soil, air: water, climate, natural or cultural heritage, other physical structure, or in general, subsequently alter environmental, social, economic, or cultural conditions;

6/ "Social" means people's lifestyles and the ways they interact with one another;

7/ "Social Impact" means the negative or positive impact of a development plan on people's lifestyles, relationships and community organization;

8/ "Licensing Agency" means any government organization that is empowered by law to issue an investment permit or a trade or operating license or a work permit or to register a business organization, as the case may be;

9/ "Project" means any development transaction of public, private, nongovernmental organization, or community asset that can be done with the intention of developing or improving the national economic and social services while ensuring future generation to have equitable use by a defined resource, at given time and place to produce products and services;

10/ "Proponent" means any government organization if the project is owned by the public sector, any person if the project is owned by the private sector or the population mentioned if it is planed with Public resources;

11/ "Public Instrument" means any government policy, law, strategy and program;

፲፪/ "የአካባቢና ማህበራዊ ይሁንታ ፈቃድ" ማለት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ በመገምገም ፕሮጀክቱ እንዲተገበር የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

፲፫/ "የአካባቢና ማህበራዊ ይሁንታ ፈቃድ ሰጪ ተቋም" ማለት የፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ነው፤

፲፬/ "ባለሙያ" ማለት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ፣ ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ወይም የአካባቢ ኦዲት ጥናት ላይ የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት በባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፲፭/ "ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ" ማለት አንድ ፕሮጀክት ከሚተገበርበት ክልል ተሻግሮ በሌላ ክልል ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ነው፤

፲፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፵፯ መሠረት የተካተተ ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ ዓላማ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፯/ "የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት" ማለት የአካባቢ ጉዳዮችን በሚመለከት በክልል መንግስት ኃላፊነት የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፡፡

፲፰/ "ባለሥልጣን" ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፲፱/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በፕሮጀክት ባለቤቶች፣ ፍቃድ ሰጭ መስሪያ ቤቶች፣ መንግስታዊ ሰነድ አመንጭዎች፣ በባለሥልጣኑ እና በክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12/ "Environmental Clearance Certificate" means a certificate issued after reviewing an environmental and social impact assessment for the implementation of the project;

13/ "Environmental and Social Clearance Issuing Organization" means the Federal Environmental Protection Authority or Regional Environmental Protection Agency;

14/ "Professional" mean individuals that obtained certificate of competency from the Authority to provide consulting services in environmental and social impact assessment, strategic environment assessment or environmental audit.

15/ Trans-Regional Impact" means an impact that transcends from the region where a project is implemented to other region;

16/ "Region" means any of those parts of Ethiopia specified as Regions under Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administration;

17/ "Regional Environmental Protection Agency" means any regional government organ entrusted by that region with a responsibility for the protection or regulation of the environment and natural resources;

18/ "Authority" means the Environmental Protection Authority;

19/ "Person" means any natural person or juridical person;

20/ Any expression in the masculine gender includes the female.

**3. <u>Scope of application</u>**

This Proclamation shall apply to project proponents, Licensing Agencies, the Authority and Regional Environment Agencies and it shall apply on all Federal and Regional public instruments.

## ክፍል ሁለት

## አጠቃላይ ግዴታዎች እና የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች

### ፬. አጠቃላይ ግዴታዎች

፩/ ማንም ሰው ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ፕሮጀክት ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ለማድረግ አይፈቀድለትም፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑሰ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ማንኛውንም ፕሮጀክት የሚከተለው ተፅዕኖ ጉልህ ያልሆነ ነው ብሎ ከገመተ የፕሮጀክቱን ባለቤት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያካሂድ ላያስገድደው ይችላል፡፡

፫/ ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የስራ ፈቃድ ከመስጠቱ እንደሁም ከማደሱ በፊት ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን የአካባቢና ማህበራዊ ይሁንታ ፈቃድ መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ተቀባይነት ማግኘቱና ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ይሁንታ ፈቃድ መሰጠቱ የፕሮጀክቱን ባለቤት በአካባቢና ማህበረሰብ ላይ ጉዳት በማድረስ ከሚከተል ኃላፊነት ነፃ አያደርገውም፡፡

፭/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከተጠያቂነት ነፃ መሆን የሚቻለው ጉዳቱ በተጎጂው በራሱ ወይም ደግሞ የፕሮጀክቱ ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሦስተኛ ወገን መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

### ፭. የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች

፩/ የፕሮጀክት ተፅዕኖ ከፕሮጀክቱ መጠን፣ ከመካሄጃ ስፍራው፣ ከባህሪዩ፣ ከክልል ተሻጋሪነት፣ ከሌሎች ተፅዕኖዎች ወይም ክስተቶች ጋር ከሚኖረው ተዳማሪነት፣ ከቆይታው፣ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ ከመቻሉ ወይም ካለመቻሉ እንደዚሁም ከሌላ ተዛማጅ ገጽታ አኳያ መገምገም አለበት፡፡

## PART TWO

## GENERAL OBLIGATIONS AND CONSIDERATIONS TO DETERMINE IMPACT

### 4. General Obligations

1/ without authorization from the Authority or from the relevant Regional Environmental Agency, no person shall commence implementation of any project that requires environmental and social impact assessment as determined in a Directive issued pursuant to this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provision of Sub Article (1) of this Article, when the Authority or the relevant Regional Environmental Agency assumes that the possible impacts of the project are insignificant, it may decide not to require the concerned proponent to conduct an environmental and social impact assessment.

3/ any licensing agency shall, prior to issuing and renewing of an investment permit or a trade or an operating license for any project, ensure having the environmental and social clearance from the authority or the relevant regional environmental agency.

4/ approval of an environmental and social impact study report or the granting of environmental and social clearance certificate by the authority or the relevant regional environmental agency does not exonerate the proponent from liability for damage.

5/ Without prejudice to Sub Article (4) of this Article, exemption from liability shall be granted only when it is verified that it is the victim himself or a third party for whom the proponent is not responsible that has caused the damage.

### 5. General Considerations to Determine Impact

1/ the impact of a project shall be assessed on the basis of the size, location, nature, cumulative effect with other concurrent impacts or phenomena, trans-regional effect, duration, reversibility or irreversibility or other related effects of the project.

፪/ ጠቃሚና ጎጂ ውጤቶች ካሉት ነገር ግን ጠቃሚ ጎኑ በትንሹ ብቻ ከሚያመዝን ወይም መብለጥ አለመብለጡ ከሚያወዛግብ አንድ ፕሮጀክት ሊከተል የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ሲወስን ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ወደ ጥንቃቄ እርምጃ በማዘንበል ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል በማለት መወሰን አለበት፡፡

2/ the Authority or the relevant Regional Environmental Agency shall on the side of caution while determining the negative impact of a project having both beneficial and detrimental effects, but which, on balance, is only slightly or arguably beneficial, and thus determine that it is likely to entail a negative significant impact.

## ክፍል ሦስት

## የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውና ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ፕሮጀክቶች እና የፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች

## PART THREE

## PROJECTS REQUIRING ENVIRONMENTAL AND SOCIAL IMPACT ASSESSMENT, TRANS-REGIONAL ENVIRONMENTAL AND SOCIAL IMPACT ASSESSMENT AND DUTIES OF A PROPONENT

### ፮. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች

፩/ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ፕሮጀክት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ማካሄድ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው መመሪያ፡-

ሀ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለማይታሰቡ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የማያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች፤ እና

ለ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለሚታሰቡ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶችን ለይቶ ማመልከት አለበት፡፡

### 6. Projects Requiring Environmental and Social Impact Assessment

1/ any project which falls in any category listed in any Directive issued pursuant to this Proclamation shall be subject to environmental and social impact assessment.

2/ A Directive provided under Sub-Article (1) of this Article shall, among other things, determine categories of:

a) projects not likely to have negative impacts, and so do not require environmental and social impact assessment; and

b) projects likely to have negative impacts and thus require environmental and social impact assessment.

### ፯. ክልል ተሻጋሪ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ

፩/ ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት በሚካሄድበት ክልል ውስጥ የሚገኝ የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባን ለባለስልጣኑ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ ባለስልጣኑ ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል የሚባሉት በሚመለከታቸው ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦች አስተያየት ተጠይቆ የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት

### 7. Trans-Regional Environmental and Social Impact Assessment

1/ the Regional Environmental Agency in the region where a project with likely trans-regional impact is being initiated shall ensure the submission of the environmental and social impact study report of the project to the Authority.

2/ the Authority shall, prior to embarking on the evaluation of an environmental and social impact study report of a project with likely trans-regional impact, ensure that the communities likely to be affected in each region have been consulted and their views incorporated.

## ፰. የፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች

፩/ አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ አካሂዶ የፕሮጀክቱን አሉታዊ ተፅዕኖዎች በቅድሚያ ለይቶና ተፅዕኖዎቹን የማስቀሪያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ ውስጥ አካትቶ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ተገቢነታቸውን ከወሰነባቸው ሰነዶች ጋር የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባውን ለባለስልጣኑ ወይም ለክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በፕሮጀክቱ ላይ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የሚያካሂደው ባለስልጣኑ በሚያወጣው ማንኛውም መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ባለሙያዎች መሆኑን የፕሮጀክት ባለቤት ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማን ለማካሄድ፣ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ለመመርመር ወይም ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልገውን ወጪ የፕሮጀክት ባለቤት መሸፈን አለበት፡፡

፬/ የፕሮጀክቱ ባለቤት በፕሮጀክቱ ጉዳት ይደርስባቸዋል ተብለው የሚገመቱትን ማህበረሰቦች ቢያንስ በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዝግጅት እና በጥናቱ ግምገማ ወቅት የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ከህብረተሰቡ አስተያየቶችን በጽሁፍ እና በቃል መቀበል ይኖርበታል፡፡

፭/ አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሲካሄድ ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ በየትኛውም ክልል የሚገኝ ማህበረሰብን ማሳተፍ አለበት፡፡

፮/ አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ሲተገብር በተሰጠው ይሁንታ ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ማሟላት አለበት፡፡

፯/ የፕሮጀክቱ ባለቤት በግሉ የሚያካሂደውን የአካባቢና ማህበራዊ ኦዲት በዘርፉ ፈቃድ ባላቸው ባለሙያዎች ማከናወን ይኖርበታል፡፡

፰/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (፯) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ግዴታዎች አሉበት፡-

## 8. Duties of a Proponent

1/ a proponent shall undertake an environmental and social impact assessment, identify the likely adverse impacts of his project, incorporated the means of their prevention or containment, and submit to the authority or the relevant regional environmental agency the environmental impact study report together with the documents determined as necessary by the Authority or the relevant Regional Environmental Agency.

2/ a proponent shall ensure that the environmental and social impact of his project is conducted and the environmental and social impact study report prepared by experts that meet the requirements specified under any Directive issued by the Authority.

3/ the cost of undertaking an environmental and social impact assessment and preparing an environmental and social impact study report shall be borne by the proponent.

4/ the project proponent shall hold at public consultations during environmental and social impact assessment and review stage to receive their oral or written comments from communities who may be deemed to be affected by the project

5/ a proponent shall carry out the environmental and social impact assessment of a project that is likely to cause a trans-regional impact in consultation with the communities likely to be affected in any region.

6/ when implementing his project, a proponent shall fulfill the terms and condition of environmental and social clearance.

7/ An environmental and social audit made by a proponent shall be carried out by a certified consultant.

8/ without prejudice to the provision of Sub-Article (7) of this Article, any proponent shall have the following obligations:

ሀ) ለኦዲት የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን፤

ለ) በይሁንታ ፈቃድ እድሳት ወቅት የኦዲት ዘገባ ማቅረብ፤ እና

ሐ) በኦዲት ግኝት የተገኘ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ለባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ፣ ምርመራ እና ይሁንታ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

### ፱. የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ

፩/ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የፕሮጀክቱን መካሄድ ወይም አለመካሄድ ተገቢነት እንዲሁም ሲካሄድ ሊኖረው የሚገባውን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችለውን በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት፡፡

፪/ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት፡-

ሀ/ የፕሮጀክቱን ባህሪ፣ በጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂና አጠቃቀም፤

ለ/ ፕሮጀክቱ ሲተገበር እንዲሁም ቋሚ ስራው ሲከናወን ወደ አካባቢ የሚለቀቀውን የበካይ ይዘትና መጠን፤

ሐ/ ለስራው እንቅስቃሴ የሚጠይቀውን የኃይል ፍጆታና ምንጭ፤

መ/ ሊከተል ስለሚችል ክልል ተሻጋሪ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ መረጃ፤

ሠ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የሚገመቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ባህሪያትና የሚቆዩበት ጊዜ፤

ረ/ አሉታዊ ተፅዕኖን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል የታቀዱ እርምጃዎች፤

ሰ/ የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ችግርን ለማቃለል የተነደፉ እቅዶች፣ የአደጋ መከላከያ ዝግጁነት፤ እና

a) cover the expenses for the audit;

b) submit an audit report while renewing license;

c) report to the Authority or competent Regional Authority on the audit investigation and measures taken.

## PART FOUR

## ENVIRONMENTAL AND SOCIAL IMPACT ASSESSMENT STUDY REPORT, REVIEW AND VALIDITY PERIOD OF CLEARANCE CERTIFICATE

### 9. Environmental and Social Impact Assessment Study Report

1/ an environmental and social impact study report shall contain sufficient information to enable the authority or the relevant regional environmental agency to determine whether and under what conditions the project shall proceed.

2/ an environmental and social impact study report shall contain, as a minimum, a description of:

a) the nature of the project, including the technology and processes to be used;

b) the content and amount of pollutant that will be released during implementation as well as during operation;

c) source and amount of energy required for operation;

d) information on likely trans-regional environmental and social impacts;

e) characteristic and duration of all the estimated direct or indirect, positive or negative impacts.

f) measures proposed to eliminate, minimize, or mitigate negative impacts;

g) plans prepared to mitigate environmental and social problems and contingency preparedness in case of accident; and

ሸ/ ፕሮጀክቱ በሚተገበርበትና እንደዚሁም ቋሚ ስራው በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ የቁጥጥርና የክትትል ስራዎች የሚካሄዱባቸውን መንገዶች፡፡

፫/ ባለስልጣኑ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ዘገባውን ለመመርመር የሚረዱ ሀሳቦችን የሚዘረዝሩ የቴክኒክ መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

**፲. <u>የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ምርመራ</u>**

፩/ ምርመራ እንዲካሄድበት ለባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የሚቀርብ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በአጭር የተዘጋጀ የጥናቱን መግለጫ የያዘ እንዲሁም የጥናቱ መረጃ መሟላትና ትክክለኛነቱን የሚያመላክት አጭር መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

፪/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ከ፵፭ የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቱን ከገመገመ በኋላ፡-

ሀ) አሉታዊ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑን ካመነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ይቀበላል፣ እንዲተገበርም ይሁንታ ይሰጣል፤

ለ) አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት ወይም በበቂ ሁኔታ ለመቋቋም የሚቻል መሆኑ ከታመነ ለማስቀረት ወይም ጉዳት ወደማያደርስ ደረጃ ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ እንዲሟሉ በማዘዝ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ ይሰጣል፤ ወይም

ሐ) ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በአካባቢና ማህበረሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስቀረት እንደማይቻል ካመነ ትግበራውን ይከለክላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትን ለመገምገም እና ውሳኔ ለመስጠት እንደፕሮጀክቱ ባህሪይ፣

h) procedures of self- auditing and monitoring during implementation and operation the project.

3 The Authority shall issue technical guidelines that determine the elements necessary to prepare as well as evaluate an environmental and social impact study report.

**10. <u>Review of Environmental and Social Impact Study Report</u>**

1/ an environmental and social impact study report that is submitted to the authority or the relevant regional environmental agency for review shall include a brief statement summarizing the study in non-technical terms as well as indicating the completeness and accuracy of the information given in the study report.

2) the Authority or the competent Regional Authority by taking into account any public comments and expert opinions shall evaluate an environmental and social impact study report within 45 working days and:

a) approve the project without conditions and issue authorization if it is convinced that the project will not causes negative impacts.;

b) approve the project and issues authorization with conditions that must be fulfilled in order to eliminate or reduce adverse impacts or reduce adverse impacts to insignificant level if it is convinced that the negative impacts can be effectively countered; or

c) refuse implementation of the project if it is convinced that the negative impact cannot be satisfactorily avoided.

3) with out prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Authority or competent Regional Authority, may extend the review and decision making period based on the nature and extent of the project.

ውስብስብነት ወይም መጠን ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ በላይ ወስዶ ሊገመግም ወይም ሊወስን ይችላል፡፡ አተገባበሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

The implementation of this Article shall be determined by the Directive issued pursuant to this Proclamation.

**፲፩. የፀደቀ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባ እና ይሁንታ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ**

፩/ የይሁንታ ፈቃድ የተሰጠው የፕሮጀክት ባለቤት በየዓመቱ ይሁንታ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይሁንታ ፈቃድ የተሰጠው የፕሮጀክት ባለቤት በየሶስት ዓመቱ የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅዱን በማሻሻል ለባለሥልጣኑ እና ለክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች አተገባበር ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**11. Validity Period of Endorsed Environmental and Social Clearance Certificate**

1/ any project proponent shall annually review the project that has received an environmental and social clearance certificate.

2/ with out prejudice to Sub-Article (1) of this Article, a project proponent that has received an environmental and social clearance certificate shall update its environmental and social management plan every three years and submit to the Authority or relevant Regional Environmental Protection Agency

3/ the implementation of Sub-Article (1) and (2) of this Article shall be determined by the Directive issued pursuant to this Proclamation.

## ክፍል አምስት

## የአዲስ ሁኔታ መከሰት፣ የትግበራ ክትትል እና ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ

## PART FIVE

## OCCURRENCE OF NEW CIRCUMSTANCE, IMPLEMENTATION MONITORING AND STRATEGIC ENVIRONMENTAL AND SOCIAL IMPACT ASSESSMENT

**፲፪. የአዲስ ሁኔታ መከሰት**

የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የጥናት ዘገባ ከቀረበ በኋላ የሁኔታው መከሰት የሚያስከትለው ውጤት ከባድ የሆነ ቀደም ሲል ያልተጤነ እውነታ ቢከሰት ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የሚያስከትለውን ውጤት ለማጤን እንዲቻል የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማው እንደአስፈላጊነቱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ማዘዝ ይችላል።

**12. Occurrence of New Circumstance**

If an unforeseen fact of serious implication is realized after the submission of an environmental and social impact study report, the Authority or the relevant Regional Environmental Agency may, as may be appropriate, order the environmental and social impact assessment to be revised or to be redone in order to address the implication.

**፲፫. የትግበራ ክትትል**

፩/ የፕሮጀክቱ ባለቤት ፕሮጀክቱን በመተግበር ላይ የሚገኘው ለፕሮጀክቱ ትግበራ ይሁንታ በተሰጠበት ወቅት በገባው ቃል እና በተጣለበት ግዴታ መሠረት መሆኑን ለመገምገም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው

**13. Implementation Monitoring**

1/ the Authority or the relevant Regional Environmental Agency shall monitor the implementation of an authorized project in order to evaluate compliance with all commitments made by, and obligations imposed on the proponent during authorization.

የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በፕሮጀክቱ አተገባበር ላይ ክትትል ማድረግ አለበት።

፪/ አንድ የፕሮጀክት ባለቤት እንዲተገብር በሚገባው ወይም ይሁንታ የተሰጠውን ፕሮጀክት በገባው ቃል ወይም በተጣለበት ግዴታ መሠረት ካልተገበረ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት መወሰድ ያለበትን የእርምት እርምጃ በመግለጽ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል።

፫/ እንደአግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም ፕሮጀክት እንዲተገበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲(፪) (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የሰጠውን ይሁንታ ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ሌላ ማንም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሰጠውን ፈቃድ ይህንኑ ውሳኔ ተከትሎ ማገድ ወይም መሰረዝ አለበት።

## ፲፬. ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ

፩/ በባህሪያቸው ቸል ሊባል የማይቻል የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ የመንግስት ሰነዶች መደብን ለመለየትና ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ባለሥልጣኑ ማውጣት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት በሚወጣው መመሪያ መደብ ውስጥ የተካተተ ማንኛውም የመንግስት ሰነድ ከመፅደቁ በፊት ሰነድ አመንጪ መንግስታዊው አካል ሰልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ በባለሙያ ማስጠናት አለበት፡፡

፫/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የፖሊሲ ወይም የሕግ ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናት ሰነድን በመገምገም ምክረ-ሀሳቡን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ይልካል፡፡

2/ when the proponent fails to implement the authorized project in compliance with the commitments he entered into or obligations imposed upon him, the Authority ·or the relevant Regional Environmental Agency may order him to undertake specified rectification measure.

3/ any other authorizing or licensing agency shall, in tandem with the authority's or the relevant regional environmental agency's decision to suspend or cancel any authorization to implement a project, suspend or cancel the license it may have issued in favor of the project.

## 14. Strategic Environmental and Social Assessment

1/ The Authority shall issue a Directive to determine the category of public instrument which are likely to cause significant environmental and social impact and define the procedure of their assessment.

2) any government organization that initiates public instrument shall have the obligation to conduct strategic environmental and social assessment on the public instrument that falls under the Directive to be issued in accordance with the Sub-Article (1) of this Article.

3) the Authority or the competent Regional Environmental Agency shall submit its recommendations of the strategic environmental and social assessment on policy or laws to the concerned government body.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፖሊሲ እና ሕጎች ውጪ ያሉ መንግስታዊ ሰነዶች በባለስልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ተገምግሞ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል ፡፡

፭/ በመንግስት ሰነዶች ላይ የሚደረግ ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናት የሚከተሉትን ጉዳዮች ታሳቢ ማድረግ አለበት፡-

ሀ) መንግስታዊ ሰነዱ ከሌሎች የሃገሪቱ የአካባቢ ሕጎች የተጣጣመ ስለመሆኑ፤

ለ) መንግስታዊ ሰነዶቹ ሊያስከትሏቸው ስለሚችሉት ድምር ተፅዕኖች፤

ሐ) ተፅዕኖዎቹ ክልል ወይም ድንበር ተሻጋሪ ስለመሆናቸው፤

መ) አካባቢያዊ ስሱነት፤

ሠ) የሚሸፍናቸው አካባቢዎች እና በተፅዕኖዎቹ የሚጎዳ የህዝብ ብዛት፤

ረ) ተፈጥሯዊ የአካባቢ ሁኔታ፤

ሰ) ማህበራዊ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን፡፡

## ክፍል ስድስት

## የኃላፊነት ክፍፍል፣ የሕዝብ ተሳትፎ ፣ የአካባቢና ማህበራዊ ኦዲት እና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

### ፲፭. የኃላፊነት ክፍፍል

፩/ ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥሩ ድርሻ የፌደራል መንግሥት አካል ከሆነ ወይም ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና ክትትል የማካሄድ ኃላፊነት የባለስልጣኑ ነው።

፪/ ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥር ድርሻ የክልል መንግሥት አካል ከሆነና ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ

4) Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article, strategic environmental and social assessments apart from policies and laws shall be reviewed by the Authority or competent Regional Environmental Agency and determine as per a Directive issued following this Proclamation.

5) the strategic and social environmental assessment of public instruments shall take into account:

a) the consistency of the public instrument with other environmental laws of the country;

b) the potential cumulative impacts of the public instruments;

c) wether impacts are inter-state or trans-boundary;

d) environmental sensitivity;

e) the area coverage and number of potentially affected people;

f) natural environmental conditions;

h) social, cultural and religious aspects.

## PART SIX

## JURISDICTION , ENVIRONMENTAL AND SOCIAL AUDIT, PUBLIC PARTICIPATION INCENTIVE AND GRIEVANCE PROCEDURES

### 15. Jurisdiction

1/ the Authority shall be responsible for the evaluation of an environmental and social impact study report and the monitoring of its implementation when the project is subject to licensing, execution or supervision by a Federal government or when it is likely to produce trans-regional impact.

2/ the Regional Environmental Agency in each region shall be responsible for the evaluation and authorization or any environmental and social impact assessment study report and the monitoring of its implementation if the

እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና አተገባበሩን የመከታተል ኃላፊነት የክልል አካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ነው።

፫/ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትላሉ ተብለው የሚታሰቡ ፕሮጀክቶች ላይ ባለስልጣኑ የይሁንታ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ስልጣን ያለውን የክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ማማከርና ሀሳብ መቀበል አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ ስልጣን ካለው አካል ጋር በጋራ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፮. ስለሕዝብ ተሳትፎ

፩/ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በዘገባው ላይ አስተያየት መጠየቅ አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት በአጠቃላዩ የሕዝብ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክቱ አተገባበር ጉዳት ያስከትልባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ማኅበረሰቦች አስተያየት በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ጥናቱ ውስጥ መካተቱን፣ እንደዚሁም ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት መጤኑን ማረጋገጥ አለበት።

፫/ የፕሮጀክቱ ባለቤት በሚያካሂዳቸው የህዝብ ውይይቶች ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት አካባቢ የሚገኙ የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ተወካዮች ተገኝተው ውይይቱን በተገቢ ሁኔታና አሳታፊነትን ጠብቆ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣሉ፡፡

፬/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናት ዘገባ እንደደረሰው ዘገባውን በሕዝብ ማስታዎቂያ አውታሮች በኩል በማሰራጨት ለአስራ አምስት የሥራ ቀናት የህዝብ አስተያየት መሰብሰብ አለበት፡፡

project is not subject to licensing, execution and supervision by a federal agency and if it is unlikely to produce trans-regional impact.

3/ the Authority shall consult and receive comments from competent Regional Environmental Agency on projects likely causing inter-state impact prior to approval.

4 Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the Authority in collaboration with competent authority shall monitor and evaluate the implementation of the project.

## 16. Public Participation

1/ the Authority or the relevant Regional Environmental Agency shall make any environmental and social impact study report accessible to the public and solicit comments on it.

2/ the Authority or the relevant Regional Environmental Agency shall ensure that the comments made by the public and in particular by the communities likely to be affected by the implementation of a project are incorporated into the environmental and social impact study report as well as in its evaluation.

3/ Representatives of the relevant Regional Environmental Agency shall participate on project area public consultation, and ensure that the comments of the communities have been well recorded as per the Directive issued pursuant to this Proclamation.

4/ The Authority or the Regional Environmental Agency shall disseminate the environmental and social impact assessment report through public notice and accept comments for 15 working days.

፭/ በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ የህዝብ ተሳትፎ ዝርዝር አፈፃፀም ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፯. ስለአካባቢና ማህበራዊ ኦዲት

፩/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የፕሮጀክቶቹ አተገባበርን በሚመለከት ቢያንስ በየሁለት ዓመቱ አንድ ጊዜ ኦዲት ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ኦዲት አድራጊው ባለስልጣኑ ከሆነ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበትን ክልል ስልጣን ያለው አካል ማሳተፍ አለበት፡፡

፫/ የኦዲት ዘገባው ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ) በፕሮጀክቱ የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መሠረት የተወሰዱ እርምጃዎች፤

ለ) የኃይል አጠቃቀም መረጃ፤

ሐ) የቆሻሻ አያያዝ፤

መ) ለአካባቢ አያያዝ ዕቅድ ትግበራ ሀብት ስለመመደቡ፤

ሠ) ሙያተኛ ቀጥረው ወይም የአካባቢ ጉዳዮችን የሚከታተል የሥራ ክፍል አቋቁመው እየሰሩ ስለመሆናቸው፤

ረ) የአካባቢ ኦዲት ማድረጋቸውና ሪፖርት ለባለስልጣኑ ወይም ለክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ስለማቅረባቸው፡፡

፬/ ኦዲት አድራጊው የሚከተሉትን መረጃዎች በሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡-

ሀ) የፕሮጀክቱን የምርት ጥራት፣ ትርፍና ኪሳራ፤

ለ) የፕሮጀክቱን ጤናማ የንግድ እንቅስቃሴ የሚጎዱ ጉዳዮች፡፡

## ፲፰. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

፩/ ለፕሮጀክት ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ ወይም በክትትል ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት ከባለሥልጣኑ ወይም ከክልል የአካባቢ ጥበቃ

5/ The detail implementation of public participation in environmental and social impact assessment study shall be determined by the Directive issued pursuant to this Proclamation.

## 17. Environmental And Social Audit

1/ the Authority or the Regional Environmental Agency shall audit the implementation of the project at least once in two years.

2/ without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Authority, if it is conducting the audit by itself, shall engage competent regional authority where the project is to be implemented.

3/ the Audit report shall contain the following information:

a) measures taken as per the environmental management plan;

b) energy consumption information

c) waste management

d) resource allocated for the environmental management

e) environmental issues follow up by employing experts or establishing an environmental unit.;

f) conducting and submitting environmental audit report to the Authority or competent Regional Environmental Agency.

4/ the Auditor shall keep the following information confidentially:

a) product quality, profit and losses of the project;

b) activities that affect the healthy business transactions.

## 18. Grievance Procedure

1/ any person dissatisfied with the authorization or monitoring or any decision of the Authority or the relevant regional environmental agency regarding

መሥሪያ ቤት በተሰጠ በማንኛውም ሌላ ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን እንደአግባቡ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት፣ የባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።

## ፲፱. ስለ ማበረታቻ

ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መሥሪያ ቤት የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ወይም ብክለትን ለማስቀረት ወይም የተበከለን ለማፅዳት ወይም የአረንጓዴ ልማትና ቴክኖሎጂን የተመለከተ የፕሮጀክት አተገባበርን አቅሙ በሚፈቅደው መሠረት ሙያዊ የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳. ስለጥፋትና ቅጣት

፩/ ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት ወይም የመንግስት ሰነድ አመንጪ የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ወይም ስልታዊ የአካባቢና ማህበራዊ ግምገማ እንደ የቅደም ተከተሉ እንዲካሄድበት የተወሰነን ማንኛውም ፕሮጀክት ወይም የመንግስት ሰነድ ከባለስልጣኑ ወይም ስልጣን ካለው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የይሁንታ ፈቃድ ሳያገኝ ፕሮጀክቱን ወደ መተግበር የገባ እንደሆነ ከ፭፻ሺ ብር በማያንስ እና ከ፲ ሚሊዮን ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ወይም በስልታዊ አካባቢና ማህበራዊ ግምገማ ጥናት ዘገባ ውስጥ የሀሰት መግለጫ ወይም መረጃ ያቀረበ እንደሆነ ከ፩፻ሺ ብር በማያንስ እና ከ፭፻ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

the project may submit a grievance notice to the head of the Authority or the relevant Regional Environmental Agency, as may be appropriate.

2/ the decision of the Head of the Authority or relevant Regional Environmental Agency shall, as provided under Sub-Article (1) of this Article, be issued within 30 days following the receipt of the grievance.

## 19. Incentive

The Authority or the relevant Regional Environmental Protection Agency may, to the extent that its capacity allows, support the implementation of a project destined to provide any environmental rehabilitation or pollution prevention or clean up or green development and technology

## PART SEVEN
## MISILANIOUS PROVISIONS

## 20. Offences and Penalties

1/ any proponent or public instrument initiator who implements a project or public instruments without obtaining the required environmental and social assessment or strategic environment and social assessment authorization respectively from the Authority or the competent Regional Environmental Protection Agency, shall be punishable with a fine not less than 500,000 Birr and not exceeding 10,000,000 Birr.

2/ any person who presents a false statement or information in the environmental and social assessment or strategic environmental and social assessment report shall be punishable with a fine not less than 100,000 Birr and not exceeding 500,000 Birr.

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሲሰጠው የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር የቀረ እንደሆነ ከ፩፻ ሺ ብር በማያንስ እና ከ፫፻ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፬/ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ሲፈፅም ድርጅቱ እንዲከፍለው ከተፈረደበት መቀጮ በተጨማሪ የሕጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባውን ተግባር በትጋት ያልተወጣ ከሆነ የሥራ የበላይ ኃላፊው ከ፶ሺ ብር በማያንስ እና ከ፩፻፶ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭/ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ሰው ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ ወደነበረበት እንዲመልስ ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ሊወስን ይችላል፡፡

፮/ በአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ መሠረት ወደ ትግበራ ያልገባ ፕሮጀክት የወንጀልና የፍትሃብሔር ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ወይም የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## ፳፩. ነባር ፕሮጀክት

ማንኛውም የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ማለፍ የሚጠበቅበት እና የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ያልተደረገበት ነባር ፕሮጅት ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የአካባቢና ማህበራዊ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለባለስልጣኑ ወይም በክልል ለአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

3/ any person who fails to keep records or to full fill the condition of authorization issued pursuant to this Proclamation shall be punishable with a fine not less than 100,000 Birr and not exceeding 300, 000 Birr.

4/ when a juridical person commits an offence, in addition to whatever penalty it may be meted with, the manager who fails to exercise all due diligence shall be liable with fine not less than 50,000 Birr and not exceeding 150,000 Birr.

5/ the Court before which a person is prosecuted for an offence under this Proclamation or Regulation or Directives emanating from it, may in addition to any penalty it may impose, order the convicted person to restore or in any other way compensate for the damage inflicted.

6/ on the project that failed to transfer to implimentation based on environmental and social impact assessment, without prejudice to the criminal and civil liability, the Authority or a Regional Environmental Agency may take Administrative measures as per a Directive issued following this Proclamation.

## 21. Existing Project

Any existing project which is expected to pass through environmental and social assessment but has not undergone the assessments hall prepare environmental and social management plan within one year beginning from the date of the coming into force of this Proclamation and submit to the Authority or the competent Regional Environmental Agency .

**፳፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ባለስልጣኑ ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፫. የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ አዋጅ አተገባበር ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፬. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

፩/ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፱/፩ሺ፱፻፺፬ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፫ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**22. Power to Issue Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation

2/ The Authority may issue Directives for the implementation of this Proclamation and the Regulation issued pursuant to this Proclamation.

**23. Duty to cooperate**

Any person or institution shall have the duty to cooperate in the implementation of this Proclamation.

**24. Inapplicable Laws**

1/ Environment Impact Assessment Proclamation No 299/2002 is hereby repealed.

2/ Any Law, Regulation, Directive or practice inconsistent with this Proclamation is inapplicable regarding matters provided herein.

**25. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazetteee.

**Done at Addis Ababa, on this 11th day of April, 2025.**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**